# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 10<br><br>Hawaasa, Arfaasa 1, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲<br><br>ሀዋሳ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |



**Amado**

**Wodhote Kiiro 10/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmanna Fayyimmate Ledo Amadantino Owaantenna *Giwaatete* Silanchimma Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho …… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣንን ስልጣንና ተግባር ለመደንገግ የወጣ ደንብ …….. ገጽ ….**


## Wodhote Kiiro 10/2013

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmanna Fayyimmate Ledo Amadantino Owaantenna *Giwaate* Silanchimma Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho**

Dagoomu fayyimmanna hobbaate agarate, hursasinna silanchimmasi buuxaminokki yannilicho ikko budu xagichinni agarama noosihura;

Co'ichimmasena silanchimmase agarantinokki sagale korkaatinni dagoomu fayyimma aana

## ደንብ ቁጥር ፲/፳፻፲፫

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣንን ስልጣንና ተግባር ለመደንገግ የወጣ ደንብ**

የሕብረተሰቡ ጤና ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ያልተረጋገጠ ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ መድኃኒት መጠበቅ ያለበት በመሆኑ፤

ደህንነቱና ጥራቱ ባልተጠበቀ ምግብ ምክንያት በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና

iillitara dandiitanno fayyimmate mitiimma gargarate, seerimale xagganna qixxaabbano amanyoote gargaranna ittisa hasiisinohura;

Fayyimmate handaarira rosame keeshshinohu billaallinonna silanchimmate xe'ne noo gashshootinna qorqorshu amanyoote bilchaatanna gumaamo assate dandiinanni gede haaronna qinaabbino: sagalete, xagichunna fayyimmate awuutishshi gashshootinna qorqorshu amanyoote lifixinoha assa hasiissannoha ikke leellinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma jeefisiisaanote amaale mini jeefisiisaano bisubba uurrisate, biilloonyenna loosu qeechansa murate fulino lallawu kiiro 3/2012 quwa 10 cinaancho quwa 12 iima uynoonnisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

1. **Harancho Umo**

   Tenne wodho "Fayyimmanna Fayyimmate Ledo Amadantino Owaantenna *Giwaate* Silanchimma Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodhote Kiiro 10/2013" yine xawinsara dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu horo wole tiro aanno gede assa hooguro tenne wodho giddo:

   1. **"Sagale"** yaa ayeeno burimasinni, bocunni woy wo'munni ra'e qixxaawino daddaloho woy wole doogonni dagate owaantera

ችግር መከላከል እና የሕገ ወጥ መድሃኒቶችንና ምርት-ሥርዓትን መከልከልና መግታት ማስፈለጉ፤

በጤናው ዘርፍ ሰፍኖ የቆየውን የተበታተነና ጥራት የጎደለውን የአስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል አዲስና የተቀናጀ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፲፪ ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ስልጣንና ተግባር ለመደንገግ የወጣ ደንብ ቁጥር ፲/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1 **"ምግብ"** ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡአ ገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ውኃ ወይም ሌላ መጠጥ፣የሚታኘክ ማስቲካ፣

shiqinsheenna mannaho sagalimmate hosannoricho ikke waa woy wole agatto, corqinanni maasitika, sagale hattono sagale qixxeessate woy xagisatenna lexxote ayeerichono sagalimmate horora hosannore hanqafanoha ikke araddonna xagichimmate horora calla hossannore diamadanno;

2. **"Sagalete Daddali Uurrinsha"** yaa sagale daddalu hajara qixxeessa, sowaa, abbisiisa, beeha, bebbeehe hira woy marro ashage hirate looso loosanno uurrinshaati;
3. **"Sagalete Uurrinsha"** yaa sagalete daddali uurrinshanna daddaloho ikkitinokki hexxonnino babbaxxitino doogonni kaa'lotenni woy owaante uytanno uurrinshanni dagoomaho uurrinshunni sagale shiqishshanno uurrinshaati;
4. **"Sagalete Keeranchimma"** yaa sagale hasiissanno doogonni qixxeessatenni, amadatenni, duunatenni, hodhisatenni woy horonsi'raanote iillishate ha'rinsho giddo sagale fayyimmate sumuu yitannota ikkase buunxanni loosu amanyooteti;
5. **"Sagale Arrishshote Caabbichira Reqecci Assa"** yaa sagale arrishshotenni kalaqamanno ayonete caabbichira reqecci assate;
6. **"Daaimu Qaaqquulli Sagale"** yaa lewu agani geeshsha noo daaimira uurrinshate sagalete hasattonsa wonshate hasiisanno deerri garinni faabirikaho qixxeessinanni sagaleeti;

ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከምና ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትንባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

2 **"የምግብ ንግድ ተቋም"** ማለት ምግብን ለንግድ ዓላማ ማምረት፣ መላክ፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ በችርቻሮ፣ መሸጥ ወይም እንደገና ማሸግ ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፤

3 **"የምግብ ተቋም"** ማለት የምግብ ንግድ ተቋምና ሌላ ከንግድ ዓላማ ውጭም ምግብን በተለያየ መንገድ በእርዳታ ወይም በአገልግሎት መስጫ ድርጅት በቋሚነት ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

4 **"የምግብ ደህንነት"** ማለት ምግብን በተገቢው መንገድ በማምረት፣ በመያዝ፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ ወይም ለተጠቃሚ በማቅረብ ሂደት ምግቡ ለጤና ተስማሚ እንደሆነ የሚረጋገጥበት አሰራር ነው፤

5 **"ምግብ ማጭረር"** ማለት ምግብን ለተወሰነ ዓይነት አዮን ፈጣሪ ለሆነ ጨረራ ማጋለጥ ነው፤

6 **"የጨቅላ ህጻን ምግብ"** ማለት እስከ ስድስት ወር እድሜ ላሉ ጨቅላ ህጻናት መደበኛ የምግብ ፍላጎታቸውን ለማሟላት አግባብ ባለው ደረጃ መሠረት በፋብሪካ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

7. **“Qaaqquullu Sagale”** yaa hasiisanno deerri garinni saadatewiinni woy mu’rotewiinni afi’nannirinni, faabirikaho qixxeessineenna sagale ikke 6 aganinni kayse 3 diri geeshsha ikkitino qaaqquullira sagalimmate faabiriku deerrinni qixxeessinannite;
8. **“Karsiisa”** yaa mitte sagalete amado woy bikka batisate, silanchimma woy kaajjille ajishate woy ledate, la”ate woyyaabbinota woy roore ikkitanno gede lawisiisate woy wole kuri labbanno hexxora yaate xaadannokkire woy amadooshshe leda woy sagalete amado wolurinni riqiwate;
9. **“Xagicho”** yaa mannaho xisso layi’rate, xagisate, xisso dilleessate, woy gargarate horora hosanna ayeereno karsiinsoonniricho ikke narkotikinna saykotiropikite xagga, pirikerserete kemikaalla budillicho xagga irkisaancho woy doorshu xagga, hadho, mundeenna mundeennire, vakisinna, caange kalaqqanno xagga, kosimotikise, co’ichimma agarate qixxeessinannirichonna xagishshu udiinne ledanno;
10. **“Badooshshu Malaate”** yaa ha’runsate yine uduunnu aana borreessinanni hurrishshu malaatinna kiiro nooha ikke uduunnichu daafira taje xawisannohu badooshshe ikke kaa’lanno dahaawino malaateeti;

7 **“የህጻን ምግብ”** ማለት አግባብ ባለው ደረጃ መሠረት ከእንስሳት ወይም ዕጽዋት ተዋጽኦ በፋብሪካ የሚመረት ምግብ ሆኖ ዕድሜያቸው ከ፮ ወር እስከ ፫ ዓመት ለሆኑ ህጻናት ምግብነት በፋብሪካ ደረጃ የሚዘጋጅ ነው፤

8 **“መከለስ”** ማለት የአንድን ምርት ግዝፈት ወይም ክብደት ለመጨመር፣ ጥራቱን ወይም ጥንካሬውን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣ እይታው የተሻለ ወይም የበለጠ እንዲሆን በማስመሰል ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር ወይም ይዘት መጨመር ወይም የምርቱን ይዘት በሌላ ንጥረ -ነገር መተካት ነው፤

9 **“መድኃኒት”** ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎች፣ የባህል መድኃኒ-ቶች፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃ-ኒቶች፣ መርዞች፣ ደምና የደም ተዋጽኦዎች፣ ቫክሲኖች፣ ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲኮች፣ የሳኒተሪ ዝግጅቶች እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤

፲ **“የመለያ ምልክት”** ማለት ለክትትል ሲባል በምርት ላይ የሚጻፍ ተከታታይ ሰረዞች እና ቁጥር ያለበት ስለምርቱ መረጃ የሚገልጽ እንደ መለያ ሆኖ የሚያገለግል የሚስጥር ምልክት ነው፤

11. **“Alkoole”** yaa ayeehano agu dana ikke alkoolete bikki amado xibbunni zeero bixxille onte anga ale ikkino agattote danaati;
12. **“Narkotike Xagga woy Saykotiropikite Qimamma’’** yaa Itophiyu sheemaaxxino Kalqete Halantino Mootimma narkotike xagga woy saykotiropikite qimamma qorqorshi sheemaati kaiminni kalqoomu deerrinni qorqorsha assinanni xagga ikke jeefisaano bisi narkotikinna saykotiropikite xagga yee su’mannoreno ledanno;
13. **“Araddote Qixxaawo’’** yaa gamu deerrinni ikko wo’munni wo’ma araddote daronni loonsannire ikke; wiliishshatenni, giddora qolle huuwatenni, corqatenni woy su’niissi’ratenni adhinannirichooti;
14. **“Shiisha”** yaa mitte woy mittete ale ikkitinota sayissanno boombe kayinsoonninna waa woy wole du’namanoricho amadino uduunne horonsi’ratenni wiliishshinannihu lexxote coommilli nooha woy nookkiha araddote mu’ro ikke kuni araddote gumi molaasese, malawo, kaashshu gilasiroole woy babbaxxitino gumma coommille lede woleno togoo amado afidhino mu’ro lede amadannoho;
15. **“Xagishshu Udiinne”** yaa mannaho xisso la’’ate woy xagisate bisu giddo woy bisu gobba mannimma horote aana hosano aye

፲፩ **“አልኮል”** ማለት ማንኛውም የአልኮል ይዘቱ ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ በላይ የሆነ የመጠጥ ዓይነት ነው፤

፲፪ **“ናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች”** ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የተባበሩት መንግሥታት የናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ስምምነት መሠረት ዓለም - አቀፍ ቁጥጥር የሚካሄድበት መድኃኒት ሲሆን አስፈጻሚ አካሉ የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ መድኃኒት ብሎ የሚሰይመውንም ይጨመራል፤

፲፫ **“የትምባሆ ዝግጅት”** ማለት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል የተዘጋጀ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ ወይም በማሽተት የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

፲፬ **“ሺሻ”** ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የማስተላለፊያ ቱቦ የተተከለበት እና ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ የያዘ መሣሪያን በመጠቀም የሚጨስ ተጨማሪ ጣዕም ያለው ወይም የሌለው የትምባሆ ምርት ሲሆን ይህ የትምባሆ ውጤት ሞላሰስ፣ ማር፣ የአትክልት ግላይሰሮል ወይም የተለያየ የፍራፍሬ ጣዕምን ጨምሮ ሌላ ይዜት ያለውን ምርት ይጨምራል፤

፲፭ **“የሕክምና መሣሪያ”** ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ አካል ላይ ጥቅም የሚውል

udiinne woy horoonsi’nanniricho ikke addi addi layi’rate, laboratoorete, dare gowate xagishsha, hinkote xagishshi udiinnenna mada gombanni heqo, sirinjuwa, marfuwa, faashsha, goze, fuuttanna wole kore lawanno qixxaawo, mannu loosino hinkuwa, kemikaalla, caangete filmuwanna woloota hakkore labbanno uduunenna horonsi’nannire ledanno;

16. **“Saniterete Qixxaawo”** yaa mannu woy mini giddo co’ichimma aga’rate horo aanno gede qixxeessinoonniricho ikke: paade, taampe, hinkote co’ichimma, hunkee cingaannorenna udiinne co’icha assi’rate woy hayishshi’rate horoonsi’nannire hanqafanno;

17. **“Budillicho Xagicho”** yaa mu’ro, saada woy shiilote loonsanniha ikke: corqinanni, anganninna riqqinanni manna ikko saadate xagishshira owaante aanno qixxaawooti;

18. **“Kosimotike”** yaa biso co’o assi’rate, biifisi’rate, xummenna wogaro lexxate, woy mannimmate suudi soorramikkinni dana biifate bisu aana buudhinanni: qiwaate, looshine, shitto, suumete kuulla, culunqate kuulanna biifannore, illenna alba biifinsi’annire, dananchu kuulla, foole su’niissannore, add addi saamunna, kuri loosate horoonsi’nannire baala kamale amadanno;

ማንኛውም መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ህክምና፣ የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎች እና የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ሲሪንጆ-ችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻ፣ ጉዝ፣ ጥጥና መሰል ዝግጅቶችን፣ ሰው ሰራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን፣ የጨረራ ፊልሞችንና ሌሎች መሰል መሳሪያዎችና መገልገያዎችን ይጨምራል፤

፲፮ **“የሳኒተሪ ዝግጅት”** ማለት የሰው ወይም የቤት ውስጥ ንጽህናን ለመጠበቂያ የሚያገለግል ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን ፓዶችን፣ ታምፖችን፣ የጥርስ ንጽሕና መጠበቂያ ዝግጅቶችን፣ የላብ መምጠጫዎችን እና ዲተርጀንቶችን ይጨምራል፤

፲፯ **“ባህላዊ መድኃኒት”** ማለት የዕጽዋት፣ የእንስሳት ወይም ሌላ የማዕድን ተዋጽኦ ሆኖ በነጠላም ሆነ በመቀላቀል ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት የሚውል ዝግጅት ነው፤

፲፰ **“ኮስሞቲክ”** ማለት ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደም ግባት ለመጨመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር በገላ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን የቆዳ ቅባቶችን፣ ሎሽኖችን፣ ሽቶዎችን፣ የከንፈር ቀለሞ-ችን፣ የጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ፣ የዓይንና የፊት ማስዋቢያ፣ የጸጉር ማቅለሚያዎችን፣ የጠረን መቀየሪያ ዝግጅቶችን፣ ሜዲኬ-ትድ

19. **“Xagichu Daddali Looso”** yaa xagga daddalu mixonni loosa, wirro xaaxa, abbisiisa, sowa, jimilunni hira woy coccolunni beeha ikkanna silanchimma qorqora, sayinsitte xiinxallo assinanni biiro uurrisanna xiinxallo assanna daddalunni riqiwammetenni loosa kamalanno;
20. **“Xagicho Hajanjanni Woraqata”** yaa fajjo noosi xagishshu ogeessi xagisi’raanote borreesse aanno xagicho qeechineenna horoonsi’nanni hajajooti;
21. **“Ikkadimmate Buuxishshi Tajete Woraqata”** yaa fulino fayyimmate qorqorshi deerri bikkaanchi garinni: sagalete, xaggate, woy fayyimmatenna fayyimmate ledo amadantino owaante woy daddali loosira bobbakkanno mannira uynanni loosu fajjooti;
22. **“Lawisiise Shiqisha”** yaa sagale woy xagicho xaanxannire, bandannire, daddalu malaate, daddalu su’ma woy ayeehano baxxino malaate horoonsi’ratenni sagale woy xagichu hattenne halaalaancho loossanno uurrinshanni loosaminohu gede lawisiisatenni woy sagalimmatenna xagichimmate amadonna akata soorre shiqishatenni mannu fayyimma aana gawajjo iillishate;
23. **“Qorqoraancho”** yaa tenne wodho garinni qorqorshu looso gumulate hajo la’annonsa bissanni biilloonye uynoonnisi

ሳሙናዎችን እና ለእነዚህ ዝግጅቶች መሥሪያ የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤

፲፱ **“የመድኃኒት ንግድ ሥራ”** ማለት መድኃ-ኒቶችን ለትርፍ ዓላማ ማምረት፣ እንደገና ማሸግ፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ በጅምላ ማከፋፈል ወይም በችርቻሮ ማደል ሲሆን ጥራት መመርመርን፣ ሳይንሳዊ ቢሮ ማቋቋምና ምርምር ማካሄድን እና በንግድ ወኪልነት መሥራትን ይጨምራል፤

፳ **“የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት”** ማለት ፈቃድ ባለው የሕክምና ባለሙያ ተጽፎ ለሕሙማን የሚሰጥ የመድኃኒ ዕደላ ትዕዛዝ ነው፤

፳፩ **“የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት”** ማለት በወጣው የጤና ቁጥጥር ደረጃ መስፈርት መሰረት በምግብ፣ በመድኃኒት ወይም በጤና ወይም በጤና ነክ አገልግሎት ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነው፤

፳፪ **“አስመስሎ ማቅረብ”** ማለት የምግብ ወይም የመድኃኒት ማሸጊያ፣ መለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም ምግቡ ወይም መድኃኒቱ በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል ወይም የምግብነት ወይም የመድኃኒትነት ይዜትና ባህርይ ለውጦ በማቅረብ በሰው ጤና ላይ ጉዳት ማስከተል ነው፤

፳፫ **“ተቆጣጣሪ”** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት

aye ogeessati;

24. **“Ishine”** yaa industirratenni, irshu darguwanni, rosu minnanni, teessote minnanni, daddalu minnanni, fayyimmatenna xiinxallote uurrinshuwanni, shumate minnanninna wolootu labbanno uurrinshubbanni fulannonna mannunna saadate fayyimma aana gawajjo iillishara dandaanno: du’namaancho, kaajjadonna wole ishineeti;
25. **“Qarqaru Fayyimma Agarate Xe’ne”** yaa mannu hee’ranno qooxeessi’ra: bisu lopho, fayyimmate woy hee’nanni heeshsho aana gawajjo iillishara dandaanno aye dani ikkitooti;
26. **“Fayyimmate Ogeessa”** yaa mannu fayyimma agarate woy owaante aate hajo la’annonsa bissanni fayyimmate ogeessi gede borreessamino manchooti;
27. **“Xagishshu Ogeessa”** yaa xissaminoha la’’atenni, xissote dana badannohonna xagichunni woy biso dare gowatenni xagisanno mannu xagisaancho woy kuri assootuwa loosate massagganno bissanni fajjinoonnisi fayyimmate ogeessaati;
28. **“Xagichu Ogeessa”** yaa hajo la’annonsa bissanni ogimmate loosi fajjo uyinoonnsi: farmaasiste, diraagiste woy farmaasete tekinishaaneeti;

የቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ባለሙያ ነው፤

፳፬ **“ቆሻሻ”** ማለት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከእርሻ ቦታዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከንግድ ስፍራዎች፣ ከጤናና ምርምር ተቋማት፣ ከመጸዳጃ ቤት ወይም ከሌሎች መሰል ተቋሞች የሚወጣና በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ፈሳሽ፣ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ቆሻሻ ነው፤

፳፭ **“የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት”** ማለት ሰው በሚኖርበት አካባቢ የሚገኝ በአካላዊ ዕድገት፣ በጤና ወይም በአኗኗር ዘይቤ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ሁኔታ ነው፤

፳፮ **“የጤና ባለሙያ”** ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስ-ጠት አግባብ ባለው አካል እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤

፳፯ **“የሕክምና ባለሙያ”** ማለት ሕመምተ-ኛውን በመመርመር የበሽታውን ዓይነት የሚለይና በመድኃኒት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሐኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን በአስፈጻሚው አካል የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፤

፳፰ **“የመድኃኒት ባለሙያ”** ማለት አግባብ ባለው አካል የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት ወይም ፋርማሲ ቴክኒሻን ነው፤

29. **"Budillicho Xagishsha"** yaa gobbate giddoha ikkinohanna rosichunni afi'noonni hattono dagoomunni adhamooshshe afidhino egenno woy ogimma ikkite mu'rote woy saadatenni anfannirinni, shiillatenni woy angate ogimma horoonsi'ratenni uynanni xagishshu owaanteeti;
30. **"Budillichu Xagishshi Xagisaancho**" yaa budillicho xagishsha aate hajo la'annonsa bissanni loosu fajjo uynoonnisi manchooti;
31. **"Ogimmate Loosi Fajjo"** yaa fayyimma agarate owaante woy woloota fiixoontanno owaante aate dandiinanni gede fayyimmate ogeessira uynannisi tajete woraqataati;
32. **"Fayyimmate Uurrinshsha"** yaa fayyimma bowirsate, dhibba gargarate, xagisatenna wirro woyyeessate loossa woy xagichu daddali looso woy owaante uytanno ayeetano: mootimmate, mootimmaame ikkitinokkinna hallanyu uurrinshaati;
33. **"Fayyimmate Ledo Amadamino Qorqorsha Assinanni Uurrinsha"** yaa ayeetano dagooma owaantanni uurrinsha ikke: rosu mini, seerunna seejjote mine, geerra kaa'linanni mereersha, maatiweelo qaaqquulle lossinanni mereersha, daaimu hoshsho, dikkote darguwa, ispoortete darguwa, xixxiiwote mereersha,

፳፱ **"ባህላዊ ሕክምና"** ማለት አገር በቀል የሆነና በልምድ የካበተ እንዲሁም በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያገኘ ዕውቀት ሆኖ የዕጽዋትን ወይም የእንስሳትን ተዋጽኦ፣ የማዕድናት ወይም የእጅ ጥበብ በመጠቀም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፤

፴ **"የባህላዊ ሕክምና አዋቂ"** ማለት ባህላዊ ሕክምና ለመስጠት አግባብ ባለው አካል የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፴፩ **"የሙያ ሥራ ፈቃድ"** ማለት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፴፪ **"የጤና ተቋም"** ማለት የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፤

፴፫ **"ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም"** ማለት ማንኛውም የኅብረተሰብ መገልገያ ተቋም ሲሆን፣ ትምህርት ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማዕከላት፣ የአሳዳጊ አልባ ህፃናት ማዕከላት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ የገበያ ቦታዎች፣ የስፖርት ቦታዎች፣ የመታሻ ማዕከላት፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የጸጉር ቤቶችና የውበት ሳሎኖችን ይጨመራል፤

gangalattote mereersha, dananchu seesi minna ledanno;

34. **“Loosu Ledo Amadaminohunni Fayyimma Agadhate Gara”** yaa loosu qooxeessira kalaqantanno woy loosu ledo fiixoomu noonsa: kemikaale, fiizikaalenna *sinehiywotaawe* ikkino gawajjannore gargaratenninna qorqoratenni loosaasine danote reqecci yitannokki gede assatenni: sayinsitte, tekinoloojetenna gashshootu hayyo horoonsi’ratenni loosaasinete fayyimma agarate dandiissiinsanni garaati;

35. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowoti;

36. **“Jeefisiisaano Bissa”** yaa qoqqowu fayyimmatenna fayyimmate ledo amadantino owaantetenna giwaatete silanchimma qorqorshi biilloonyeti;

37. **“Dayrekitere”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma fayyimmatenna fayyimmate ledo amadantino owaantenna giwaate silanchimma qorqorshi biilloonyi dayrekitereti;

38. **“Hajo La’annonsa Bissa’’** yaa hasiishshisi garinni qoqqowu biilloonye woy fayyimmatenna fayyimmate ledo amadantino owaantenna *giwaate* silanchimma qorqorsha assitanno gede biilloonye uynoonninsa quchumu gashshoote woy woradu gashshooteti;

39. **“Mancho”** yaa kalqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso

፴፬ **“ሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ”** ማለት በሥራ አካባቢ የሚከሰቱ ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ኬሚካላዊ፣ ፊዚካላዊና ሥነ ሕይወታዊ ጎጂ ንጥረ ነገሮች በመከላከልና በመቆጣጠር ሠራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ ሳይንሳዊ፣ ቴክኖሎጂያዊና አስተዳደራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሠራተኞችን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሳይንስ ነው፤

፴፭ **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤

፴፮ **“አስፈጻሚው አካል”** ማለት የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ነዉ፤

፴፯ **“ዳይሬክተር”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ዳይሬክተር ነው፤

፴፰ **“አግባብነት ያለው አካል”** ማለት እንደ አግባቡ የክልሉ ባለስልጣን ወይም የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር እንዲያደርግ ስልጣን የተሰጠው የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ አስተዳደር ነው፤

፴፱ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፵ **“ቢሮ”** ማለት የክልሉ ጤና ቢሮ ነው፤

፵፩ **“የፌደራል ባለሥልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

uynoonnisiho;

40. **“Biiro”** yaa Qoqqowu Fayyimmate Biiroti;
41. **“Federaalete Biilloonye”** yaa Itophiyu sagalete, xagichunna fayyimmate qorqorshi biilloonyeti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu wole koo-teemmano hanqafanno.

**4. Jeefishshi Mami-geeshsha**

Tini wodho qoqqowu giddo afantanno baalante qarqarrara loosu aana hossanno.

**5. Hundaanchimma**

Biilloonyu Qoqqowu Fayyimmate Biiro hundaanni galanno.

**6. Qara Borro Mine**

Biilloonyunnihu qaru borrote mini Hawaasi Quchumira ikke hasiishshu garinni gashshootu taqqubara sinu borrote minna heedhasira dandiitanno.

**7. Hexxo**

Biilloonyu Hexxo:

1. Sagalete co’immanna silanchimma;
2. Xagichunnita keeraanchimmasi, hursannoha ikkasi, silanchimmasinna garunni horoonsi’ramasi;
3. Fayyimmate, xagishshunna xagichu ogeeyyeta ogimmatenna akatoomete ikkadimma;

**፫ የፆታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ጾታ የተደነገገው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፬ የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም አካባቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፭ ተጠሪነት**

የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለክልል ጤና ቢሮ ይሆናል፡፡

**፮ ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለስልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በየአስተዳደር እርከኖቹ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**፯ ዓላማ**

የባለሥልጣኑ ዓላማ፡-

1 የምግብ ደህንነትና ጥራትን፤
2 የመድኃኒት ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀምን፤
3 የጤና፣ የህክምናና የመድኃኒት ባለሙያዎችን ሙያዊና የስነ-ምግባር ብቃትን፣
4 የጤና ተቋሞችን ድርጅታዊ ብቃትን፣ እና
5 የሀይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ለግልና ለሕብረተሰብ ጤና ተስማሚ መሆኑን

4. Fayyimmate uurrinshuwa tantanote ikkadimmanna;
5. Meessinna qarqaru fayyimma agarranni gari annu annuna dagoomu fayyimmara sumuu yaannoha ikkasi buuxa ikkitanno.

**8. Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Biilloonyeho aane noo biilloonyinna loosu qeechi hee’rannosi:

1. Sagale, xagichunna fayyimmate owaante gashshate, qorqoratena gumulsiisate fultino woloota seerubba, wodhubbanna biddisubba loosu aana hosansa buuxannonna qorqoranno.
2. Sagale, xagichunna fayyimmate owaante gashshootenna qorqorsha gumulsiisate fultino woloota seerubba, wodhubbanna biddissubba loosu aana hosiisate qorqoraano gaamanno.
3. Sagallate co’ichimmanna silanchimma, xaggate co’ichimma, hursansa, silanchimmanna garunni horoonsi’ramase, fayyimmate ogeeyye owaante uytanno garanna ogimmate akatoome, meessi keeraanchimmanna qarqaru fayyimmate agarooshshi xe’ne fayyimmanna fayyimmate ledo amadantino qorqorsha assinanninsa uurrinshuwa qorqorshu looso loosanno.
4. Hajo la’annosi bisi narkotiketenna saykotropikete xagga owaante uytanno uurrinshuwa: xissamaanote hajaja, beeha,

ማረጋገጥ ይሆናል።

**፰ ሥልጣንና ተግባራት**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1 የምግብ፣ የመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለማስፈጸም የወጡ ሌሎች ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

2 ምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለማስፈጸም የወጡ ሌሎች ሕጎችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፤

3 የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም፣ የጤና ባለሙያዎችን የአገልግሎት አሰጣጥና የሙያ ስነ ምግባር፣ የሀይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ተቋማትየ ቁጥጥር ሥራዎችን ይሠራል፤

4 አግባብ ያለው አካል የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች አገልግሎት ላይ በሚውሉባቸው ተቋማት ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይቆጣጠራል፣ አለአግባብ መጠቀምን

horoonshu gara, maareekkamanna rippoorte assa qorqoranno; garimale horoonsi'ra hoolanno; horoonsha lainohunni federaalete biilloonyiranna hajo la'annonsa bissara rippoorte assanno.

5. Mootimmate, mootimmaame ikkitinokki fayyimmate uurrinshubara xaphoomunna umi dirimi hosipitaallara fayyimmate xaawubbara, fayyimmate keelluwara, kiliinikuwate, xaggate coccolu daddali uurrinshubba, medikaale laboratoorrara, diyagonasiki immeejingete, sagalete owaante uytanno uurrinshuwaranna, qorqorsha assinanninsa fayyimmate ledo amadantino uurrinshuwa ikkadimmate buuxishshi tajete woraqata uytanno; haaroonsitanno; cuffanno; ittissanno; taje rigiddanno;
6. Qoqqowu giddo: sagalete, xagichunna qarqaru fayyimma agarooshshi, fayyimmate ogeeyyenna fayyimmanna fayyimmate ledo amadamino qorqorsha assinanninsa uurrinshuwa lainohunni mashalaqete mereersha ikke kaa'lanno woy owaante aanno;
7. Sagalete woy xagichu hadhaawa woy daafama korkaatinni iillanno: reyote, fayyimmate mitiimma kora ikkitannore addi addi akeekka haa'ratenni la'nanni gede sowanno; mayimmansa buuxanno; anfanni gumi garinni hasiissanno qaafo adhanno;

ይከላከላል፣ አጠቃቀምን አስመልክቶ ለፌደራሉ ባለስልጣንና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤

5 ለመንግስት፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ጤና ተቋማት፣ ለጠቅላላና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ጤና ኬላዎች፣ ክሊኒኮች፣ የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች፣ ሚዲካል ላቦራቶሪዎች፣ ዲያግኖስቲ ኢሜጅንግ፣ የምግብ አገልግሎት መስጫ ተቋማትና ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ጤና ነክ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያሽጋል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

6 በክልሉ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉን ተቋማት በሚመለከት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

7 በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል ለምርመራ ይልካል፣ ምንነታቸውን ያረጋግጣል፣ በዉጤቱም መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

8 የትምባሆ ዝግጅትን፣ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን፣ የሚሸጡ ወይም የሚቸረችሩ ድርጅቶችን ማስተዋወቅን፣ አስተሻሸግንና መለያ አሰጣጥንና አወጋገድን ይቆጣጠራል፣

8. Araddote qixxaawo hirranninna horoonsi'nanni gari, hirtanno uurrinshuwa egensiisa, xaanxanni garanna badooshshu malaate aate garanna kayisiisate gara qorqoranno; adha hasiissanno qaafo adhanno.
9. Qoqqowu giddo taraawanno dhibbi kalaqamiro, ikkadu gargaratenna gaaramate loosi loosamino gede buuxanno; hasiissanno qaafo adhanno;
10. Qoqqowu giddo fayyimmate owaante loosi aana bobbakkino fayyimmate ogeeyyera ogimmate fajjo aanno; ogimmate akatoome agadhite loossanni noo gede buuxanni haaroonsanno; ittisanno; rigidanno; federaalete biilloonyinni ogimmate maareekkonna fajjo uynanninsa fayyimmate ogeeyye, doorshunna irkishshu xagishshi ogeeyyera ogimmate fajjonsa haroonsidhanno gede irkote borro aanno;
11. Horoonsi'nanni yannansa guddino sagalla, xagganna eote udiinne garunni kayisiisamansa buuxanno;
12. Babbaxxitino uurrinshuwanni fultanno kaajjadonna du'namaancho ishine kayinsanninna hunnanni gari dagoomu fayyimma aana gawajjo iillishannokkiha ikkasi buuxanno; qorqoranno; hajo la'annonsa bissa ledo ikkatenni hasiissanno qaafo adhanno; qinaawe loosanno;

አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል፤

9 በክልሉ ውስጥ የወረርሽኝ በሽታ ሲከሰት አስፈላጊ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ መካሄዱን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

፲ በክልሉ ዉስጥ የጤና አገልግሎት ስራ ላይ ለሚሰማሩ የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሙያ ስነ-ምግባራቸውን ጠብቀው ስለመስራታቸው እያረጋገጠ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤ በፌዴራሉ ባለሥልጣን የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ለሚሰጣቸው የጤና ባለሙያዎች፣ ለአማራጭና ተደጋጋፊ ሕክምና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃዳቸዉ እንዲታደስ የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤

፲፩ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪ ከተለያዩተ ቋማት የሚወጡ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሕዝብ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አሰፈላጊውን ዕርምጃ ይወስዳል፣ በቅንጅት ይሰራል፤

፲፫ ሕገ-ወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችንና የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

፲፬ ለህብረተሰቡ የሚቀርብ የመጠጥ ውኃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

13. Seerimale sagalla, xagganna fayyimmate owaante qorqoranno; hasiissanno qaafo adhanno;
14. Dagoomaho shiqinshanni anganni way silanchimma deerra agadhinoha ikkasi buuxanno;
15. Dikkote shiqqanno: sagalla, xagganna xagishshaho owaante aanno udiinne federaalete biilloonyinni maareekkamansa qorqortanno; buuxxanno;
16. Qoqqowu deerrinni fayyimmate ledo amadantino qorqorsha assinanninsa uurrinshuwa garunni meessinsanna qarqaru co'ichimma agarooshshi bikaancho guutisansa buuxanno; qorqoranno; hasiissanno qaafo adhanno;
17. Budillichu xagishshi ogeeyyera ikkadimmate buuxishshi tajete woraqatanna ogimmate fajjo aanno; qorqoranno; seeru garinni hasiissanno qaafo adhanno;
18. Loosu ledo amadantino fayyimmate agarooshshe qorqoranno; hasiissanno qaafo adhanno;
19. Hirate shiqqino aye sagale, xagicho mannaho sagalimmate woy xagichimmate sumuu yinokkiha ikkasi buuxiro woy dagoomu fayyimma aana gawajjo iillishshanno hadhaame kemikaale seeru garinni gamba assanno; garunni kayisiinsoonnita woy hunnoonnita

፲፫ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦች፣ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በፌደራሉ ባለስልጣን መመዝገባቸውን ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፤

፲፬ በክልል ደረጃ የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፭ ለባህል ህክምና አዋቂዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ በህጉ መሰረት አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፮ የሥራ ነክ ጤና አጠባበቅን ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፱ ለሽያጭ የቀረበው ማንኛውም ምግብ፣ መድኃኒት ለሰው ምግብነት ወይም መድኃኒትነት የማይስማማ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንደሚያስከትል የታመነበትን አደገኛ ኬሚካል በህግ መሰረት ይሰበስባል፤ በአግባቡ መወገዱንም ያረጋግጣል፤

፳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመካከለኛ፣ የቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ የጤና ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በተግባር እንዲለማመዱ ወደ ጤና ተቋማት እንዲሰማሩና በአግባቡ ልምምድ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

፳፩ በክልሉ የሚከናወኑ የምግብ፣ የመድሃኒትና

buuxanno;

20. Hajo la’annonsa bissa ledo ikkatenni mereerima, maassote albiidinna maassote gedeniidi fayyimmate rosaano rossanno roso wo’naalshunni rossanno gede fayyimmate uurrinshuwara bobbakkinoronna garunni wo’naalsha assansa hoogansa qorqoranno; buuxanno;
21. Qoqqowu giddo loosantanno: sagalete, xagichunna fayyimmate owaante daddalu egensiishshuwa aana qorqorshu looso loosanno; hasiisiha ikkiro qaafo adhanno;
22. Jajjaho anna ikkanno; sheemaate sheemaaxxanno; umisi su’minni kassasanno kassasamanno;
23. Hexxo gumulate kaa’litanno woloota loossa loosanno.

**9. Biilloonyu Tantano**

Biilloonyeho Mootimmatenni mootonsinanni Qaru Dayrekiterichinna hasiishshu garinni Layinki Dayireekiterichi hattono loosoho hasiissanno loosasine heedhanosi.

**10. Qaru Dayrekiterichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Qaru Dayrekiterichi biilloonyu qara loosu jeefisaancho ikke biilloonyu looso massaganno, gashshannonna qorqoranno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 hunda xawinsoonihu xaphoomu quwi agaramino gedeenni hee'reenna qaru dayireekiterichi:
   a) Tenne wodho quwa 8 hunda

የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያዎች ላይ የቁጥጥር ስራዎችን ይሰራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፳፪ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ይከሰሳል፤

፳፫ ዓላማውን ለመፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፱ የባለስልጣኑ አደረጃጀት**

ባለስልጣኑ በመንግስት የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዳይሬክተር እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፲ የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1 ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለስልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ የተመለከቱ የባለስልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለስልጣኑን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

xawinsooonni biilloonyu biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno;

b) Biilloonyu istiraateejike mixo, diru mixo, loosu pirograamenna baajeete qixxeesse haja la'ano bisira shiqishanno, fajjiiniro loosu aana hosiisanno;

c) Biilloonyeho fajjinoonni baajeetenna loosu pirograame garinni womaashsha fulo assanno, shallago loosanno;

d) Qoqqowunnita mootimmate loosaasine seeru wodhi-woro kaima assatenni mootimmate muronni kaajjanno seera horonsi'ratenni biilloonyu loosaasine gaamanno, wole wiinni abbanno, gashshanno; geegeesanno;

e) Sayikki wogane ledo assinanni xaadooshshira biilloonye riqiwanno;

f) Biilloonyu loosu jeefishshanna shallagote rippoorte qixxeesse haja la'anona bissara shiqishanno;

g) Wolootu haja la'anonsa bissanni uyinanisi looso loosano.

3. Loosu bilchaantera hasiisanno deerrinni biilloonyisinna loosu qeechisi aaninni gama booce wolootu biilloonyu sooreyyeranna loosaasinera lekkishunni aara dandaanno.

**11. Layinki Dayrekiterichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Biilloonyu tantano garinni loosu ha'rinsho

ሐ) ለባለስልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፤

መ) የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያዛውራል፤ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለስልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለስልጣኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

ሰ) ሌሎች አግባብ ካላቸው አካላት የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

3 ዋና ዳይሬክተሩ ለባለስልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለስልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፩ የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1 በባለስልጣኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ሂደት ይመራል፡፡

2 ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ ሲወከል ተክቶት ይሰራል፡፡

3 ተጠሪነት ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፡፡

massaganno.

2. Qaru dayrekiterichi nookki woy loosara dandaannokki yannara iso riqiwe loosanno.
3. Qaru dayrekiterichira hundaancho ikkanno.

**12. Qorqoraanote Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Tenne wodho quwa 8 cinaancho quwa 2 garinni gaamantino qorqoraanora aane noo biilloonyinna loosu qeechi noonsa:

1. Qoqqowu giddo afantanno fayyimmanna fayyimmate ledo amadantino uurrinshuwa fano ikkitanno ayee yannarano qorqortanno; hasiissanno qaafo adhitanno;
2. Fayyimmate mitiimma kalaqara dandaannori ikkanni no yitanno mashalaqqe heedhunsaro, ayee hooweno woy mineno yoote mini fajjonni eatenni fonqolchitanno;
3. Qorto buuxate woy mashalaqe gamba assate hasiisannoha ikke leeliro, huluullammoonni sagalenna xagga aaninni akeeka adhate, viidiyo hinkiilate, fotogiraafe kaysate, taje foto koppe assatenna qorto buuxante goofa geeshsha fayyimmate aana gawajjo abbanno yine bidhantoonni udiinne bande hoollanni gede hajajanno; cufisiisanno;
4. Karsiisantino,*balaashaino*, awaawurantino, burquqantino woy wolu korkaatinni horonsiraanote aana gawajjo abbitanno yine huluullamoonni sagallanna xagga aana

**፲፪ የተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተመደቡ ተቆጣጣሪዎች የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

1 በክልሉ የሚገኙ የጤናና ጤና ነክ ተቋማትን ክፍት በሆኑበት በማንኛውም ሰዓት ይቆጣጠራሉ፣ አስፈላጊውን ዕርምጃ ይወስዳሉ፤

2 ጤናን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል የሚያሰኝ መረጃ ሲኖራቸው ወደ ማንኛውም ግቢ ወይም ቤት ወይም ህንጻ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመግባት ፍተሻ ያደርጋሉ፤

3 ምርመራ ለማድረግ ወይም መረጃ ለመሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተጠረጠሩ ምግቦችና መድኃኒቶች ላይ ናሙና ልኮ የመውሰድ፣ በቪዲዮ የመቅረጽ፣ ፎቶ ግራፍ የማንሳት፣ መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ የማድረግ እና ውጤቱ እስከሚታወቅ ድረስ በጤና ላይ ጉዳት ያስከትላል ተብሎ የታመነ ዕቃ ወይም ማቴሪያል ተለይቶ እንዲቀመጥ ያዛሉ፣ ያሽጋሉ፤

4 የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣ የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብሎ የተጠረጠሩ ምግቦችና መድኃኒቶች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ የማድረግና ውጤቱ

laboratoorete qorqorisha assinanni gede assatenna gumu leella geeshsha horote aana hossannokki gede cufante keeshshitanno gede assitanno;

5. Sagallanna xaggate owaante yannansa gudduro woy tenne wodho garinni horote aana hossannokki gede gumulo uyiniro, hasiisanno garinni kayinsanni gede qorqortanno;
6. Ayeno buuxo assinanni fayyimmate urrinshubba giddo loossanno fayyimmate ogeeyyewiinni mashalaqe xa’mate, la’ate, qorqorsha assatenni, buuxatenni hasiissanno qaafo adhitanno;
7. Meessi keeraanchimmanna qarqaru co’ichimma aana qorqorsha assitanno; hasiissanno qaafono adhitanno.

**13. Baajeete**

Biilloonyeho aante noo baajeettete bu’a heedhannosi:

1. Qoqqowu mootimmanni gaammanni baajeette;
2. Woloota bu’anni afi’ranno eo.

**14. Baajeettete Diro**

Biilloonyunnihu baajeettete diri qoqqowu mootimma baajeettete diro ikkanno.

**15. Shallagote Tajenna Shallagote Qorto**

1. Biilloonyu wo’manna halaalaancho shallagote taje amadanno.
2. Biilloonyu shallagotenna woxe la’anno

እስከሚታወቅ ድረስ አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ፤

5 ምግቦችና መድኃኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሲወሰን በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ይቆጣጠራሉ፤

6 በማናቸውም ቁጥጥር በሚደረግባቸው የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎችን መረጃ በመጠየቅ፣ በማየት፣ በመመርመር፣ በማረጋገጥ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳሉ፤

7 የሃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ቁጥጥር ያደርጋሉ፤አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

**፲፫ በጀት**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት የበጀት ምንጮች ይኖሩታል፤

1 ከክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፤
2 ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገቢ፡፡

**፲፬ የበጀት ዓመት**

የባለሥልጣኑ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

**፲፭ የሒሳብ መዛግብትና የሒሳብ ምርመራ**

1 ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2 የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ

tajubba qoqqowu Qara Odiitenni woy Qara Odiitenni somantanno odiiterootinni qorantanno.

**16. Halamate Gadacho**

Ayee manchino tenne wodho jeefisiisate halamate gadacho noosi.

**17. Jeefishshu Nookki Seeranna Asoote**

Tenne wodho ledo kiphi yanno aye seeri woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubba lainohunni jeefishshu diheerenosi.

**18. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Biiro tenne wodho loosu aana hosiisate hasiissanno biddissubba fushshate dandiitanno.

**19. Wodho Loosu Aana Hosanna Yanna**

Tini wodho Maaja 1 barri 2012 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Arfaasa 1, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma**

**Pirezidaanticha**

ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

**፲፮ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፯ ተፈጻሚነት የሌለው ሕግና አሰራር**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮው ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፱ ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

**ሀዋሳ፣ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ለዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**